ሊዳነ ምሕረት

ቁጥር 22

በእንተ ታቦት

<u>ኪዳነ ምሕረት</u>፡- የምሕረት ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዘላለማዊ ምሕረት እንድናገኝ የረዳን የክርስቶስ ስም ነው፡፡ ታላቁን ምሕረት ያገኘነው በእርሱ ሞት ብቻ ነውና፡፡

ማውጫ

ቀዳሚ ነገር....3
ታቦት በብሉይ ኪዳን....4
ታቦት ምንድን ነው?....4
የቃል ኪዳኑ ታቦት አሠራር....4
ጽላት....4
የታቦቱ አገልግሎት....5
ለምን የቃል ኪዳን ታቦት ተባለ?....5
ታቦቱ ለማን ተሰጠ?....5
ታቦት በዐዲስ ኪዳን....6
የተዛባ መልእክት የተሰጠው ጥቅስ....7
ኢየሱስ ታቦት ስለመባሉ....7
እውን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታቦት አለን?....7
በሲኦል እንዳትወድቁ የሙሴን ሕግ አስቡ....9
ለመዳን ዋናው ነገር ታቦት ነው....10
ያልተጻፈ ማንበብ....11
በዐዲስ ኪዳን ታቦት የበለጠ ክብር ነው የተሰጠው....12
ታቦትና ጣዖት....13
«ይላል»....14
ታቦት በሰማይ....14
ካህኑ መልአክ....15
የቃል ኪደኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷልን?....16
ታቦት ለምን በዛ?....18
ማጠቃለያ....19
ታቦታችን (ሥነ ግጥም)....19

ኪዳነ ምሕረት

በ«ማኅበረ እስጢፋኖስ ኢትዮጵያዊ» የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት የሚታተም መንፈሳዊ መልእክት ነው::
የመልእክት ሳጥን ቁጥር 29783
ዐዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Like us: www.facebook.com/ኪዳነ ምሕረት

የወልድያው ወዳጃችን በገዛ ስልክህ በተደጋጋሚ ደውለህ ስለሰጠኸን ጠቃሚ መረጃዎች ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ ብድራቱን ሁሉ ይክፈልህ!!!

ቀዳሚ ነገር

መጽሐፍ ቅዱሳችን ብሉይ እና ዐዲስ በተሰኙ በሁለት ኪዳናት የተከፈለ መጽሐፍ ነው፡፡ እነዚህ ኪዳናት የየራሳቸው ታሪክና ዳርቻ አላቸው፡፡ የቀደመው ኪዳን በእንስሳት ደም የጸና፣ መካከለኛው ሙሴ የነበረ፣ በርካታ ካህናት የተሰለፉበት፣ ሕግጋትን የያዘ፣ ኪዳኑን የተቀበሉ ሕዝቦች የነበሩት ነው፡፡

ሙሴ እንደ መካከለኛነቱ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ትእዛዛት ወደ ሕዝቡ (ሕዝበ እስራኤል) አምጥቶ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን እንዲፈጽሙ ያደረገ ሲሆን ይህን ለማድረግ የእንስሳ ደም በመርጨት ነበረበት፡፡ በዚህም ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን መግባታቸውን አወጀ፡፡ እግዚአብሔር አምላክ በሙሴ አማካይነት ለሕዝቡ የተሰጠውን ትእዛዛት የሚያስፈጽሙና በትእዛዛቱ መሠረት መሥዋዕት የሚያቀርቡ በርካታ ካህናትም ነበሩ፡፡

የእነዚህ ሁሉ መኖር ግን እንዲሁ በከንቱ ሳይሆን ሕዝቡን የሚያደርሱበት ስፍራ ነበራቸው፡፡ ያም ምድረ ርስት ከነዓን ነበር፡፡ ምንም እንኳ ሕዝቡ ከነዓን ከገቡም በኋላ ትእዛዛቱን መጠበቅ ባይቀርላቸውም የሙሴ ተልእኮ ሕዝቡን ምድራዊውን ርስት ማውረስ ነበር፡፡ በጉዞ ላይ ሳሉ በመበደሉ ምክንያት እንኳን ሌላውን ሊያወርስ ለራሱም ሳይገባ ቀረ እንጂ፡፡

ዐዲሱ ኪዳንም እንዲሁ የራሱ መልክና ጠባይ አለው፡፡ የዐዲሱ ኪዳን መካከለኛ እንደ ቀደመው ኪዳን እንደ ሙሴ በበደል ምክንያት ሕዝቡን ሊያደርስ ካለበት የረፍት ስፍራ ሳያደርስ ቀርቶ እርሱ ራሱ በመንገድ ላይ የሚሰናበት ሳይሆን ሁሉን ለእግዚአብሔር ልጅነት ማብቃት የተቻለው መካከለኛ ነው፡፡

በኢየሱስ አማካይነት እግዚአብሔር ከሕዝበ ክርስቲያን (በኢየሱስ በማመን ክርስቲያን ከሆኑቱ) ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል፡፡ እንደ ቀደመው ኪዳን ሁሉ ይህም ኪዳን የጸናው በደም ነው፡፡ የቀደመው ኪዳን በእንስሳ ደም ሲጸና ዐዲሱ ኪዳን ግን ሕያውና ቅዱስ በሆነው በጌታችን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው የጸናው፡፡

ዐዲሱ ኪዳን እንደ ቀደመው ኪዳን ሁሉ ካህን ያለው ሲሆን ከቀደመው ኪዳን የሚለየው የቀደመው ኪዳን ካህናት በአገልግሎታቸው እንዳይቀጥሉ ሞት ያቋርጣቸው ስለ ነበር በርካታ ካህናት ነበሩ፡፡ የዐዲሱ ኪዳን ካህን በሞት የማይሸነፍ፣ ሞትን ድል ያደረገ የትንሣኤ ጌታ በመሆኑ አንድ ካህን ብቻ ነው ያለው፡፡

የቀደመው ኪዳን ዳርቻ ምድራዊ ሲሆን የዐዲሱ ኪዳን ዳርቻ ሰማዊ ነው፡፡ ይህም መንግሥተ እግዚአብሔር ነው፡፡ በቀደመው ኪዳን የነበሩት ሰዎች የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሲባሉ የዐዲሱ ኪዳን ሰዎች ግን የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠርተዋል፡፡

የሁለቱም ኪዳን ሰጪ እግዚአብሔር አምላክ የቀደመው ኪዳን ለሕዝቡ ምንም እንዳልጠቀመ ባየ ጊዜ የተሻለውን ኪዳን በልጁ በኩል በመስጠት የቀደመውን ኪዳን አስቀረ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስረግጦ ቢያስተምርም ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ይልቅ የተሻለ አድርገው ያስቀመጡ ሰዎች የቀደመውን ኪዳን መልሰው ለማምጣት ሲተጉ ይታያሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ የሆኑት «መምህር» ዘበነ ለማ በቅርቡ የለቀቁት ስብከት ክርስቲያኑን ማኅበረሰብ አይሁዳዊ ለማድረግ የሠሩት ሥራ አሳይቷል፤ በዚህ የኪዳነ ምሕረት ዕትም ይህ ቀርቧል፡፡

አንብበውት ሊያነበው ለሚገባው በመስጠት አገልግሎታችንን ይደግፉ!

ታቦት በብሉይ ኪዳን

ታቦት ምን ማለት ነው ?

ታቦት የሚለውን ቃል ሊቁ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ «መርከብ ሣጥን ሙደየ ምጽዋት ሙደየ ምዉት… የቁም ሣጥን፤ ዐሥርቱ ቃላት የተጻፉባቸው የሁለቱ ጽላት ማኅደር» በሚል ፈተውታል (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ ገጽ 892)። በዕብራይስጡ ቴብሀህ የሚለው ቃል የኖኅ መርከብን እና ሙሴ ወደ ባሕር የተጣለበትን የደንገል ሳጥን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በግእዝ ታቦት በእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱሶች ደግሞ Ark በማለት ተቀምጧል። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ግን መርከብ እና ሳጥን የሚል ነው የሚነበበው። ታቦት የሚለው በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረው ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር በተያያዘ ነው።

የቃል ኪዳኑ ታቦት አሠራር

ርዝመቱ = ሁለት ክንድ ተኩል (1 ሜትር ከ25 ሳ.ሜ.)፣ ወርዱ = አንድ ክንድ ተኩል (75 ሳ.ሜ.)፣ ቁመቱ = አንድ ክንድ ተኩል (75 ሳ.ሜ.)።

ታቦት የተሠራው እግዚአብሔር አስፈላጊ ነው ብሎ በማዘዙ ስለሆነ፤ የአሠራር ሁኔታውም እርሱ እንደ ወደደው መሆን ነበረበትና፤ ለሙሴ «በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ» የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቶት ነበር (ዘጸአት 25÷40)። ለሙሴ እንዲሠራ የተሰጠው ትእዛዝም፤ በውስጥና በውጭ በጥሩ ወርቅ እንዲለብጠው፣ በእርሱም ላይ በዙሪያው የወርቅ አክሊል እንዲያደርግ፣ አራት የወርቅ ቀለበቶችም በአራቱ እግሮቹ ላይ ማለትም በአንድ ወገን ሁለት ቀለበቶች፥ በሌላው ወገን ሁለት ቀለበቶች እንዲያደርግ፣ መሎጊያዎችንም ከግራር እንጨት ሠርቶ በወርቅ እንዲለብጣቸውና ለታቦቱ መሸከሚያ በታቦቱ ጐን ባሉት ቀለበቶች መሎጊያዎቹን አስገብቶ ካስቀመጠ በኋላ መሎጊያዎቹ ከታቦቱ ቀለበቶች በፍጹም እንዳይወጡ፣ ታቦቱም ውስጥ የምስክሩን ጽላት እንዲያስቀምጥና ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ የስርየት መክደኛ ሠርቶ ሁለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ በላዩ ላይ ካደረገ በኋላ በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ እንዲያደርገው ነበር (ዘጸአት ምዕራፍ 25)። ሙሴ እግዚአብሔር እንዳሳየው እንዲሠራ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታልና ይህ እንዲህ ቢሆን ያ እንደዚህ ቢደረግ በሚል የራሱን ማስተካከያ እና ማሻሻያ ሳያደርግ እንደታዘዘው ሠርቶ ጨርሷል።



ጽላት

ጽላት ማለት ሰሌዳዎች ማለት ነው። አንዱ ጽሌ የሚባል ሲሆን ከአንድ በላይ ሲሆን ጽላት ይባላል። እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ኪዳን በገባበት ጊዜ የሰጣቸው ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፈበት የቃል ኪዳኑ ሰነድ በመሆኑ የኪዳን ጽላት ተብሏል። የጽላቱም ቁጥር ሁለት ብቻ ሲሆኑ በእነርሱ አምሳል ሌሎች ጽላት እንዲቀረጹ አልታዘዘምና ሙሴም ሆነ ከዚያ በኋላ የተነሡ ሰዎች

ተጨማሪ ጽላትን ስለ ማዘጋጀታቸው መጽሐፍ ቅዱስ ምንም አይናገርም፡፡ ምክንያቱም ለአንድ ውል አንድ የውል ሰነድ ብቻ ነውና የሚያስፈልገው፡፡

አንዳንዶች በተሰበረው ምትክ እግዚአብሔር አምላክ ሌላ ጽላት ሥራ ብሎታልና እኛም ታቦት መቅረጻችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት ይዳዳቸዋል፡፡ ሙሴ «ሁለት የድንጋይ ጽላቶች» ጠርቦ እንዲያመጣ የታዘዘው በፊተኞቹ ምትክ እንጂ የቀድሞዎቹ እያሉ ሌላ እንዲጨምር አለመሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል (ዘጸአት 34÷1)፡፡

<u>የታቦቱ አገልግሎት</u>

1. *ዕቃ ማስቀመጫ ነበረ*
   ታቦቱ ዐሥርቱ ትእዛዛት የተጻፈባቸው ጽላት፣ መና የያዘች የወርቅ መሶብ እና የበቀለች የአሮን በትር በውስጡ ይዟል (ዕብራውያን 9÷4)፡፡ ዐሥርቱ ትእዛዛት ሕዝቡ እና እግዚአብሔር የተግባቡት ቃል ኪዳን በመሆኑ ትእዛዛቱን የያዘው ታቦት በመካከላቸው ሲሆን ከእግዚአብሔር ጋር የተግባቡትን ቃል ኪዳን ዘወትር እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል፡፡
2. *መሥዋዕት ማቅረቢያ ነበረ*
   ቀደም ሲል የቀረቡት ነገሮች ታቦቱ ውስጥ ከገቡ በኋላ ታቦቱ ይከደን የነበረው በስርየት መክደኛው ነው፡፡ በስርየት መክደኛው ላይም «የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል» ነበሩበት (ዕብራውያን 9÷5)፡፡ ሊቀ ካህኑ በዓመት አንድ ጊዜ ለሕዝቡና ለራሱ የሚሆነውን የኀጢአት ማስተሰረያ ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት የያዘውን ደም በዚህ የስርየት መክደኛ ላይ በመርጨት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምሕረት እንዲያደርግ የሚጠይቅበት ነው፡፡

በዚህ ታቦት ውስጥ የተቀመጡት የድንጋይ ጽላት የብሉይ ኪዳን ወይም የቀድሞው ኪዳን ውል ምስክሮች ስለሆኑ ከብሉይ ኪዳን ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ብሉይ ኪዳን እና ታቦት ተነጣጥለው ሊታዩ አይችሉም። ለዚህ ነው ታቦቱ ራሱ "የኪዳን ታቦት" ወይም "የምስክር ታቦት" እየተባለ የሚጠራው።

- «በእርሱም ውስጥ **<u>የምስክሩን ታቦት</u>** ታኖራለህ፥ ታቦቱንም በመጋረጃ ትጋርዳለህ» (ዘጸአት 40÷3 አጽንዖት የግል)፡፡
- «ሙሴ የእግዚአብሔርን **<u>ቃል ኪዳን ታቦት</u>** የሚሸከሙትን ሌዋውያንን እንዲህ ብሎ አዘዘ» (ዘዳግም 31÷25 አጽንዖት የግል)፡፡

<u>ለምን የቃል ኪዳን ታቦት ተባለ?</u>

ታቦቱ «የቃል ኪዳን ታቦት» መባሉ እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በሲና ተራራ በገባውን ኪዳን ምክንያት ነው። «የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበላቸው፤ እነርሱም፦ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም አሉ» (ዘጸአት ምዕራፍ 21)፡፡ ታቦቱ ይህ የኪዳን ሰነድ የተቀመጠበት ማኅደር በመሆኑ የቃል ኪዳኑ ታቦት በሚል ተጠርቷል፡፡

<u>ታቦቱ ለማን ተሰጠ?</u>

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደተባለው ታቦቱ እግዚአብሔርና ሕዝበ እስራኤል ቃል ኪዳን የገቡበት ሰነድ ነው (ሮሜ 9÷4)፡፡ ስለዚህ ይህ ታቦት ከሕዝቦች መካከል የሚመለከተው ሕዝበ እስራኤልን ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የፈጸመው ከዓለም ሕዝብ ጋራ ሳይሆን ከእስራኤል ሕዝብ ጋራ ብቻ ነውና፡፡ በኪዳኑ ላይ ያለውን ትእዛዛት ሰምተው እናደርጋለን ብለው ቃል የገቡትና ኪዳኑ የጸናበትን ደም የተረጩት እነርሱ ናቸው። የቃል ኪዳኑም መታሰቢያ ሐውልቶች የተሠሩት ለእሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ነው።

> ሙሴም መጣ ለሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃሎች ሁሉ ሥርዓቱንም ሁሉ ነገረ **ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ድምፅ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ሁሉ እናደርጋለን ብለው መለሱ**። ሙሴም የእግዚአብሔርን

ቃሎች ጻፈ ማለዳም ተነሣ፥ ከተራራውም በታች መሠዊያን፥ **አሥራ ሁለትም ሐውልቶች ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ሠራ**። የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርቡ፥ ለእግዚአብሔርም ስለ ደኅንነት መሥዋዕት በሬዎችን እንዲሠዉ የእስራኤልን ልጆች ጐበዛዝት ሰደደ። ሙሴም የደሙን እኵሌታ ወስዶ በቆሬ ውስጥ አደረገው የደሙንም እኵሌታ በመሠዊያው ረጨው። የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበላቸው እነርሱም፦ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም አሉ። **ሙሴም ደሙን ወሰዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ አለ** (ዘጸአት 24÷3-8)።

ይህ የብሉይ ኪዳን ታቦት እና አገልግሎቱ ከክርስቶስ መምጣት በኋላ አስፈላጊ ባለመሆኑ ምክንያት ቀርቷል። ምክንያቱም ኢየሱስ የዓለምን ሕዝብ የራሱ ያደረገው በቀደመው ኪዳን ሳይሆን በዐዲስ ኪዳን ነውና። በብሉይ እና በዐዲስ ኪዳን መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው አስቀምጦታል፤

- ❖ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕጉ የተጻፈው በጽላቱ ላይ ነበረ በዐዲስ ኪዳን ግን በአማኞች ልብ ላይ ተመዝግቧል (ዕብራውያን 8÷10)። ስለዚህም ሐዋርያው ክርስቲያኖች የልብ ጽላት እንጂ የድንጋይ ጽላት የላቸውም ይላል (2ኛ ቆሮንቶስ 3÷3)።
- ❖ የክርስቲያኖች አገልግሎት በመንፈስ እንጂ በፊደል አይደለም (2ኛ ቆሮንቶስ 3÷6)
- ❖ የብሉይ አገልግሎት የሞት ነበረ የአሁኑ ግን የጽድቅ ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 3÷9)
- ❖ የታቦቱ አገልግሎት የሚሻር ነበረ የአሁኑ አገልግሎት በመንፈስ ስለሆነ አይሻርም (2ኛ ቆሮንቶስ 3÷11)።
- ❖ ከበፊቱ ኪዳን የአሁኑ ኪዳን አብዝቶ ይበልጣል (2ኛ ቆሮንቶስ 3÷11)።

እግዚአብሔር አስቀድሞ የታቦቱ አገልግሎት እንደማይኖር በግልጽ በትንቢት አስነግሮ ነበረ፦

> በበዛችሁም ጊዜ በምድርም ላይ በረባችሁ ጊዜ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በዚያ ዘመን፦ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም ልብ አያደርጉትም፥ አያስቡትምም፥ አይሹትምም፥ ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም (ኤርምያስ 3÷16)።[1]

ታቦት በዐዲስ ኪዳን

ዐዲሱ ኪዳን ከጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ የጸና ኪዳን ነው። ዐዲስ የኪዳን ከብሉይ ኪዳን በእጅጉ የሚለይ መሆኑን ፊተኛውን አስረጅቶአል፤ አሮጌና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ፊተኛው ኪዳን ማለትም ስለ ብሉይ ኪዳን አራት መሠረታዊ ጉዳዮችን ያነሣል እነርሱም፤

1. አርጅቷል፣
2. አሮጌ ሆኗል፣
3. ውራጅ ሆኗል፣
4. ሊጠፋ ቀርቧል። በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳን አገልግሎት በዐዲሱ ኪዳን ተተክቷል (ዕብራውያን 8÷13)።

ይህ ሐሳብ በአንድምታው ላይ እንዲህ ተብራርቷል «እሥርዕ ሕገ ዐዲስ ማለቱ እንግዳ ሥርዓት ይሠራ ዘንድ ስለ ወደደ ነው። የቀደመችው ብልየት ነበረባትና። አንድም እንግዳ ሥርዓት ይሠራ ዘንድ ወዶ እሠርዕ ሕገ ዐዲስ ማለቱ የቀደመችው ብልየት ስለነበረባት ነው። እንደሆነ ታወቀ ተረዳ። እንኪያስ ይህ ያለፈው ሕግ ጥንቱንም ለኅልፈት ቀርቦ ኖሯል ይህ ያማረ ያጌጠ ነበር ሊፈርስ ቀርቧል። ይህ ልብስ የሞቀ የደመቀ ነበር። ሊያልቅ ቀርቧል እንደ ማለት ነው» (የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት አንድምታ ገጽ 437)።

[1] ይህን ጥቅስ በተመለከተ «የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷልን?» በሚለው ስር መጠነኛ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

<u>የተዛባ መልእክት የተሰጠው ጥቅስ</u>

ብዙ ጊዜ ታቦት በዐዲስ ኪዳን አለ ብለው የሚያስቡ ወገኖች የሚጠቅሱት ጥቅስ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» የሚለውን የጌታችንን ንግግር ሲሆን ጥቅሱ ግን ስለ ታቦት በፍጹም አይናገርም (ማቴዎስ 5÷17)። ክርስቶስ በሕግና በነቢያት ስለ እሱ የተነገሩ ትንቢታትን ልፈጽማቸው ነው የመጣሁት አለ፤ መጥቶም ፈጸማቸው። «እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው» (ሉቃስ 24÷44) ተብሎ እንደተጻፈው።

ቀደም ሲል ታቦት የተሰጠው ለእስራኤላውያን ብቻ መሆኑን ተመልክተናል የኪዳኑ አካል እነሱ ነበሩና። ዐዲሱ ኪዳን ግን እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋራ ብቻ ሳይሆን ከመላው ዓለም ጋር ነው ኪዳን የገባው።

> በዚያ ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ። አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል (ኤፌሶን 2÷12-13)።

በማለት ቅዱስ ጳውሎስ በፊት ለቃል ኪዳኑ እንግዶች እንደ ነበርን አሁን ግን በኢየሱስ ዘለዓለማዊ ደም መቅረባችንን ያስረዳል።

በብሉይ ኪዳን ሙሴ የኪዳኑን ደም ለኪዳኑ ባለቤቶች ረጭቶአቸው እንደ ነበረ ሁሉ በክርስቶስ የተመሠረተው ዐዲሱ ኪዳን የእግዚአብሔር በግ በሆነው በኢየሱስ ቅዱስ ደም ተረጭተናል፦

> የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀድሱ ከሆኑ፥ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን? (ዕብራውያን 9÷13-14)።
>
> የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል (ዕብራውያን 12÷24)።

<u>ኢየሱስ ታቦት ስለመባሉ</u>

አባ ኤፍሬም፦

- ✓ ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኩለሄ ዘግብር እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ይትሜሰል ለነ ዘእግዚአብሔር ቃለ ዘኮነ ሰብአ። ትርጉም፦ በሁለንተናው በወርቅ የተለበጠ ከማይነቅዝ እንጨት የተሠራ ታቦት ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃልን ይመስልልናል (የእግዚአብሔር ቃል የተባለው ኢየሱስ ነው) - ውዳሴ ማርያም ዘእሑድ አንቀጽ 3።

ሊቁ ቄርሎስ፦

- ✓ ወእምድኅረ ኮነ ሰብእ ተሰምየ ወመሢሐ ወኢየሱስሃ ወታቦት ወዐራቁ ወበኩረ ለዘሰከቡ ወበኩረ ለዘይትነሣእ እሙታን ወርእሰ ሥጋሃ ለቤተክርስቲያን ወካልኣን አስማት ዘከመዝ ይታለው። ትርጉም፦ ሰው ከሆነ በኋላም ብእሲ መሢህ ኢየሱስ ታቦት አስታራቂ በኩር ከሙታን ወገን ለሚነሳ በኩር የምዕመናን ገዢ ፈጣሪ ተባለ እንዲህ ያሉ ሌሎች ስሞችም ይነገሩለታል (ሃይማኖተ አበው መምዕራፍ 81 ክፍል 52 ቁጥር 8)።

<u>እውን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታቦት አለን?</u>

የመጽሐፍ ቅዱሱን ታቦት መሠረት በማድረግ ቤተ ክርስቲያናችን ታቦትን አዘጋጅታ ለአምልኮት መፈጸሚያ ታደርገዋለች። ለዚህ ድርጊቷ ድጋፍ እንዲሆኗት የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን የድጋፍ ጥያቄ ታቀርብላቸዋለች።

ከቃለ እግዚአብሔር ጥቅስ መጥቀስና መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ማለት ሐሰተኛ የሆነውን ትምህርታቸንን እውነተኛ አያደረገውም፡፡ እንዲህ ያለው ተግባር «መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ» እንደሚባለው ያለ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በቤተ ክርስቲያን ታቦት አለን? ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጥ የሚገኘው መልስ የለም የሚል ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ቀደም ባለው ክፍል ውስጥ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ያዘዘው የታቦቱ እና የጽላቱ አሠራር ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አለ ከሚባለው ታቦት ጋራ በይዘትና በአሠራር ፈጽሞ የተለያየ ነውና፡፡

ምንም እንኳን አንዳንዶች ለአገልግሎት እንዲመች ነው ታቦቱ በቁመትም በክብደትም ያነሰው በማለት ምክንያት ቢያቀርቡም ይህም ንግግራቸው በፈቃደ እግዚአብሔር የተሠራውን ታቦት አሳንሰንና አቅልለን እንድንሠራ ማን ፈቀደልን? የሚል ጥያቄ ያስነሣል፡፡ ምክንያቱም አምላክ ከሰጠው መስፈርት ውጪ እኛ ለአገልግሎት እንዲመች ብለን በፈለግነው ልክ ለመሥራት ፈቃዱን የሰጠን መብቱን የለገሰን ልማዳዊው ሃይማኖታችን እንጂ ሁሉን ቻዩ አምላክ አይደለምና፡፡

ማስተዋል ያለብን ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ የታቦቱን አሠራር ከነገረው በኋላ እኔ እንዳሳየሁህ እንድትሠራ ተጠንቀቅ በማለት በማስጠንቀቂያ ጭምር እንዳዘዘው እንረዳለን (ዘጸአት 25÷40) ይህን ማስጠንቀቂያ ችላ በማለት እንዳሻን ብንሠራ የአምላክ ወዳጅ ሳንሆን ጠላት መሆናችን መታሰብ አለበት፡፡

ቀሳውስቱ እየተሸከሙ የሚወጡት ታቦት በሰው አስተሳሰብ እና ፍላጎት የተሠራ እና ያለ አቅሙ ስመ ታቦትን የተሸከመ የፍጡር የእጅ ሥራ ውጤት እንጂ የሥላሴ ፍላጎትም እቅድም አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እንግዲህ የክርስቶስ አካል የአማኞች ስብስብ በሆነች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለፍጡር ሥራ መስገድን ስታዩ አንባቢ ያስተውል ንስሐም ይግባ፡፡

እግዚአብሔር ያዘዘው የቃል ኪዳኑ ታቦት	በፍጡር ፈቃድ የተሠራው የኢትዮጵያው ታቦት
ታቦቱ የጽላቱ ቤት ማደሪያ ነው	ታቦትም ጽላትም የሚባለው አንድ ነው
የታቦቱ መጠን ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል (1 ሜትር ከ25 ሳ.ሜ)፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል (75 ሳ.ሜ)፣ ቁመቱ አንድ ክንድ ተኩል (75 ሳ.ሜ)	ታቦትም ጽላትም በሚል ስም የሚጠራው ሰሌዳ ቁመቱ አንድ ክንድ ከስንዝር ጎኑ አንድ ክንድ ውፍረቱ ሦስት ጣት፡፡[1]
በጽላቱ ላይ የተጻፈው ዐሥርቱ ትእዛዛት ብቻ ናቸው (ዘጸአት 32÷16)	የሚጻፍበት የእግዚአብሔር ስም፤ የጻድቃን ስም፤ የተለያዩ ስእላት፣ የተቀረጸበት ዘመን፣ የቁሰ ገበዙ ስም፣ የርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ስም ወዘተ.
በታቦቱ ውስጥ ሦስት ዕቃዎች አሉ (ዕብራውያን 9÷4)	እንደ ማስቀመጫ ሳጥን ሆኖ የተዘጋጀ ባለመሆኑ ምንም ዕቃ መያዝ አይችልም፡፡
ታቦቱን ዐራት ካህናት ይሸከሙት ነበረ	አንድ ካህን ብቻ ይሸከመዋል
በፍልስጥኤማውያን የተማረከበት ጊዜ ቢኖርም ወደ አገሩ ሲመለስ እንደ ረከሰ ተቁጥሮ ዳግመኛ መቀደስ አላስፈለገውም (1ኛ ሳሙኤል 4÷11)	ታቦቱ ቢሰበር ቢሰረቅ ወይም ቢማረክ እንደ ረከሰ ስለሚቈጠር ዳግመኛ መቀደስ እንዳለበት በፍትሐ ነገሥት ላይ ተደንግጓል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ለራቀውና ታቦትን በተመለከተ ላለው ትምህርቷ ድጋፍ የሚሆናት ነገር ስላጣች እያደረገችው ያለችው ነገር አልምት ባይ ተጋዳይ ነው ያስመሰላት፡፡ በዚህ መስመር ውስጥ ሰተት ብለው ከገቡት አንዱ «መምህር»[2] ዘበነ ለማ ናቸው፡፡ «መምህሩ» «የሙሴን ሕግ

[1] ደስታ ተክለ ወልድ፣ ዐዲስ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (ዐዲስ አበባ፣ 1962) ገጽ 1250፡፡ አግዛቸው ተፈራ (ዲያቆን)፣ አልተሳሳትንምን? (ዐዲስ አበባ፣ ጥር 2003) ገጽ 45፡፡

[2] «መምህር» ዘበነ ለማ «መምህርነታቸው» የክርስቶስን ወንጌል ለተራቡና ለተጠሙ ሰዎች ማድረስ አለመሆኑን የአደባባይ ላይ ስብከታቸው ይመሰክራል፡፡ የዚህ መልእክት አዘጋጆች ከክርስቶስ ውጪ የሚሰበኩና በሕዝቡ

አስቡ» በተሰኘው ስብከታቸው የተለያዩ እንግዳ ትምህርቶችን በማስተማር መጽሐፍ ቅዱስን ለገዛ ፈቃዳቸው እንዴት እንደሚያጣምሙ በአደባባይ አሳይተዋል፡፡ ከዚህ በታች ከአንደበታቸው የወጣውን ኑፋቄ መሠረት በማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ቀርቧል፤

<u>በሲኦል እንዳትወድቁ የሙሴን ሕግ አስቡ</u>

«መምህር» ዘበነ ለማ ክርስቲያኑን ማኅበረሰብ ወደ ቀደመው ኪዳን በመመለስ ክርስትናውን አስትተው አይሁዳዊ ለማድረግ ሳይፈልጉ አይቀሩም፡፡ እንዲህ የተባለው፤

የሙሴ ሕግ የእግዚአብሔር ሕግ ነው፡፡ ይህንን ራሱ የሚናገረው እግዚአብሔር ነው የሙሴን ሕግ አስቡ ይላል፡፡ <u>እንዳትጠፉ፣ በሲኦል እንዳትወድቁ፣ በዘላለም ሲቃይ እንዳትሰቃዩ፣ ከሚመጣው መከራ ከአስደንጋጩ መቅሰፍት ትድኑ ዘንድ የሙሴን ሕግ አስቡ</u>፡፡ <u>ይህ ቃል በሚልኪያስ ምዕራፍ ዐራት ቁጥር ዐራት ላይ የሚገኝ በገጽ 719 ላይ ያለ እነሆ የነቢዩ ሚልኪያስ ትንቢት የእግዚአብሔር ቃል ነው</u>

ከሚለው ንግግራቸው በመነሣት ነው (4፡21-5፡27 ደቂቃ - አጽንዖት የግል)፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ሕገ ሙሴ እና ሕገ ወንጌል አለ፡፡ «መምህሩ» ትኩረታቸው ሕገ ሙሴ ላይ በመሆኑ ስለ ሕገ ወንጌል ምንም ያሉት ነገር የለም፡፡ በዚህ በመጀመሪያው ንግግራቸው ሁለት ስሕተቶች ሠርተዋል፡፡ ስሕተታቸው ሕገ ወንጌልን አለመስበካቸው ወይም ሕገ ሙሴን ለማስተማር መቆማቸው አይደለም፡፡

የመጀመሪያው ስሕተታቸው በትንቢተ ሚልኪያስ ምዕራፍ ዐራት ቁጥር ዐራት ላይ ያልሰፈረ ነገር እንዳለ በማስመሰል ማነብነባቸው ነው፡፡ በትንቢቱ ላይ የሰፈረው *«ለእስራኤል ሁሉ ሥርዓትንና ፍርድን አድርጌ በኮሬብ ያዘዝሁትን የባሪያዬን የሙሴን ሕግ አስቡ»* የሚል ሲሆን ቀጣዮቹን ቁጥሮችንም ጨምረን እንመልከት ቢባል እንኳ *«እነሆ፥ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል»* የሚል ብቻ ነው የሚገኘው፡፡ ታዲያ «መምህሩ» ከኪሳቸው ያወጡትንና ለኑፋቄ ትምህርታቸው እንዲመቻቸው *«እንዳትጠፉ፣ በሲኦል እንዳትወድቁ፣ በዘላለም ሲቃይ እንዳትሰቃዩ፣ ከሚመጣው መከራ ከአስደንጋጩ መቅሰፍት ትድኑ ዘንድ የሙሴን ሕግ አስቡ»* በሚል የጨመሩትን የእግዚአብሔር ቃል ለማስመሰል *«ይህ ቃል በሚልኪያስ ምዕራፍ ዐራት ቁጥር ዐራት ላይ የሚገኝ በገጽ 719 ላይ ያለ እነሆ የነቢዩ ሚልኪያስ ትንቢት የእግዚአብሔር ቃል ነው»* በሚል ማቅረባቸው ስሕተት አይደለምን? በርካታ ሰዎች ፊት ቁመው እንዲህ ያለ ንግግር ማድረጋቸው ከዚህ ባስ ሲልም ይህ ስሕተታቸውን ሳያርሙ በምስለ ትዕይንት (በቪሲዲ) አሳትመው ማስራጨታቸው መቼም ሕዝቡ መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ በመመልከት አያረጋግጥም ከሚል ድፈርት የመነጨ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ሁለተኛው ስሕተታቸው ደግሞ ከሲኦል ለመዳን ወደ ዘላለም ሲቃይ ከመውደቅ ለመትረፍ ከአስደንጋጩ መቅሰፍት ለመሸሸግ እና ላለመጥፋት የሙሴን ሕግ ማሰብ አስፈላጊ እንደሆነ የተናገሩበት ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ከዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ ድረስ ያነበበ የመጽሐፍ ቅዱስ ደቀ መዝሙር ይህን የእርሳቸውን ሐሳብ የሚደገፍ ምንም ዓይነት ጥቅስ ማግኘት አይችልም፡፡ እርሳቸውም የሚደግፋቸው ጥቅስ ማግኘት ስላልቻሉ ነው በሚልኪያስ መጽሐፍ ላይ የሌለውን አለ ለማሰኘት *«ይህን እግዚአብሔር የተናገረው በነቢዩ በሚልኪያስ አማካኝነት ነው»* በሚል ብቻ የዘጉት፡፡

ቀደም ሲል እንደተባለው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ክርስቲያን የሆነውን ሕዝብ ከክርስትናው ነጥለው ወደ አይሁዲነት ሊቀላቅሉት የቋመጡት «መምህር» ዘበነ ይህን ሐሳባቸውን የሚያጠናክርላቸውን ሐሳብ እንዲህ በሚል አቅርበውት ነበር፤

መካከል ኑፋቄ የሚዘሩ ሰዎችን «መምህር» ብሎ መጥራት ከኢ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርታቸው ጋር መተባበር ነው ብለን የምናምን በመሆኑ «መምህር» የሚለውን በትምኅርተ ጥቅስ ውስጥ በማስመቀጥ የመጽሐፍ ቅዱስ «መምህር» አለመሆናቸውን ይፋ አድርገናል፡፡

በነቢዩ በሚልኪያስ የተነገረን ምንድን ነው? ምጽአት ሲመጣ በመጨረሻ የፍዳ ሰዓት መዳን የምትቸሉት በኮሬብ ለሙሴ ያዘዝኩትን ሕግ ሰትጠብቁ ነው ይላል፡፡... ምጽአት ከመምጣቱ አሰቀድሞ ሰዎች ከፍርድ እንዲድኑ የባሪያዬን የሙሴን ሕግ አሰቡ ነው ያለው እግዚአብሔር፡፡ እነሆ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድ ቀን ይመጣል፡፡ ትዕቢተኞችና ኀጢአተኞችን እነሆ የሚባላ እሳት [ይመጣል]፡፡ እናንተን ስሜን የምትፈሩ የጽድቅ ጸሐይ ይወጣላችኋል፡፡ የዚያን ጊዜ ለእስራኤል ሁሉ ሥርዓትና ፍርድን አድርጉ በኮሬብ ያዘዝሁትን የባሪያዬን የሙሴን ሕግ አሰቡ፡፡ ይህ ቃል የሚያመለክተው የመጨረሻዋን የምጽአት ሰዓት ነው፡፡ በዚያን ሰዓት ከመከራ እንድትድኑ ከሚመጣው መከራ እንድታመልጡ እኔ ለባሪያዬ ለሙሴ የሰጠሁትን ሕግ አሰቡ

የሚል መልእክት ያስተላልፋሉ (43፡28-43፡42፡፡ 50፡46-51፡38፡፡ ዘ፡35-ዘ፡46 ደቂቃ)፡፡

እስከምናውቀው ድረስ ቤተ ክርስቲያናችን ቤተ ክርስቲያን የሆነችው የአይሁድን ሕግ በመያዝ መዳን አለ ብላ ስለምታምን ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን መዳን ይገኛል ስለምትል ነው፡፡ እርሳቸውም የዚህች ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደሆኑ ይናገራሉና ክርስቲያን ናቸው ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ አሁን የተናገሩትን ነገር የተመለከተ ሰው ግን ክርስትናቸውን ቢጠራጠርና ይሁዲነትን ተቀበሉ እንዴ? ቢል ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡

ብሉይም ሆነ ዐዲስ የሙሴን ሕግ በመጠበቅ (እንደ እርሳቸው አባባል በማሰብ) መዳን እንደሚገኝ አያስተምሩም፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን የሰው ልጅ ይድን ዘንድ ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ምድር መምጣት እንዳስፈለገው ታስተምራለች፡፡ ከክርስቶስ መምጣት በፊት የነበሩና የሙሴን ሕግ በመጠበቅ የተመሰገኑት ሰዎች እንኳን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳላገኙ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ይመሰክራሉ፡፡ ከእነርሱ ሁሉ ቀድሞ ገነት መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት የታደለው ከጎኑ ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ ነው ብላም ታምናለች፡፡[1] እነርሱ የሙሴን ሕግ ከመጠበቅ ውጪ ምርጫ ስላልነበራቸው የሙሴን ሕግ በመጠበቅ ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ሲተጉ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን የሚገኝ ክርስቲያን መዳን በእግዚአብሔር ወልድ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት እያስተማሩት፣ አንድንም ሰው ለመቀደስ ያልቻለውን ሕገ ሙሴን ማሰብ ለመዳን ሁነኛ መንገድ ነው የሚል የስሕተት ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስገባ እንዴት እንዲህ ልቡ ይቋምጣል? ይህስ የሕዝቡን ልብ ከክርስቶስ ላይ በማንሣት ሰዋዊ ወደ ሆነ ነገር ለማዞር የተበተነ አረም አይደለምን?

<u>ለመዳን ዋናው ነገር ታቦት ነው</u>

ቀደም ሲል የሙሴን ሕግ ማሰብ ለመዳን አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ሲናገሩ የነበሩት «መምህር» አሁን ደግሞ፤

ስለዚህ በዛች ሰዓት <u>ለመዳን ከተሠጠ አንዱ ዋናው ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ታቦት ማክበርና በእሱ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው</u>፡፡ ተመልከቱ ስለዚህ ቃጥታ የእግዚአብሔር ቃል <u>የሚናገረው ይህንን ነው</u>፡፡ እንዲህ ነው ያለው «ለእስራኤል ሁሉ ሥርዓትንና ፍርድን አድርጉ በኮሬብ ያዘዝሁትን የባሪያዬን የሙሴን ሕግ አሰቡ» (15፡00-15፡35 ደቂቃ - አጽንዖት የግል)

በሚል ለመዳን ዋናው ነገር ሕግ ሳይሆን ታቦቱ ነው የሚል ሐሳብ ያቀርባሉ፡፡ በቅድሚያ የሐሳብ ለውጥ ሲያደርጉ ቢያሳውቁ መልካም ነበር፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል ለመዳን የሚያስፈልገው የሙሴን ሕግ «ማሰብ» ነው ብለው ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ታቦቱን ማክበርና እግዚአብሔርን በታቦቱ አማካይነት ማምለክ ነው የሚል ነገር ጨመሩ፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ለመዳን ማድረግ ያለበት የትኛውን ነው ማለታቸው ይሆን?

[1] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት (ዐዲስ አበባ፣ 1988) ገጽ 122-123፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው (ዐዲስ አበባ፣ 1988) ገጽ 432፡፡ ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር)፣ ርቱዓ ሃይማኖት (ዐዲስ አበባ፣ 2004) ገጽ 223-226፡፡ ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን (ዐዲስ አበባ፣ 2007 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 80-81፡፡

ሌላው ደግሞ ይህንን መልእክታቸውን ያስተላልፉት እንደተለመደው ጥቅስ በማጣመም ነው፡፡ እርሳቸው ይረዳኛል ብለው የጠቀሱትና *«ለእስራኤል ሁሉ ሥርዓትንና ፍርድን ኤድርጌ በኮሬብ ያዘዝሁትን የባሪያዬን የሙሴን ሕግ አስቡ»* በሚል በሚልክያስ ላይ የሰፈረው መልእክት ሐሳብ ሰዎች ታቦትን በማክበርና እግዚአብሔርን በታቦቱ በማምለክ ለመዳን የሚሆን ሊያውም ዋና ነገር መሆኑን ኢያስተምርም፡፡ ታዲያ የጥቅሱ መልእክት ምንድን ነው?

ሚልክያስ ይህን መልእክት ያስተላለፈው አይሁዳውያን ከባቢሎን ምርኮ ተመልሰው ሀገራቸውን ማቅናት በጀመሩበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን በሕዝቡ መካከል ከነበረው ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች ውስጥ የእግዚአብሔርን ስም ማቃለል አንዱ ነው (ምዕራፍ ፩ ቁጥር 6)፡፡ ይህ ድርጊታቸው ደግሞ *«የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና»* የሚለውን የሙሴን ሕግ የሚጻረር ነበር (ዘጸአት 20÷7)፡፡ ሌላው መሥዋዕታቸው እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ማለትም ዕውር፣ አንካሳ እና የታመመ ነበር (ምዕራፍ ፩ ቁጥር 8) ይህም ደግሞ በዘዳግም 15÷21 ላይ *«ነውረኛ ወይም አንካሳ ወይም ዕውር ቢሆን፥ ወይም አንዳች ክፉ ነውር ቢኖረው፥ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አትሠዋው»* ተብሎ የታዘዘውን የሚሽር ድርጊት ነበር፡፡

ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በቀጥታ እግዚአብሔር አምላክ በሙሴ አማካይነት የሰጠውን ሕግጋቱን እየተቃወሙ በመሆኑ እግዚአብሔርም ሕግጋቱን በማስታወስ ንስሐ ይገቡ ዘንድ ጥሪ ለማድረግ *«ለእስራኤል ሁሉ ሥርዓትንና ፍርድን ኤድርጌ በኮሬብ ያዘዝሁትን የባሪያዬን የሙሴን ሕግ አስቡ»* ማለት አስፈለገው፡፡ ታዲያ መምህር ከሙሉ የትንቢቱ መልእክት ውስጥ አንዲቱን ቁጥር ብቻ ቦጭቀው ሲወስዱ ሌላውን ታሪክ ምነው ዘነጉትሳ?

<u>ያልተጻፈ ማንበብ</u>

«መምህር» ዘበነ የራሳቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ሳያሳትሙ አይቀሩም፡፡ እስከ አሁን ለመመልከት እንደተሞከረው ለንግግራቸው ድጋፍ እንዲሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስን ሲጠቅሱ ወይ ያለ መልእክቱ በመናገር አልያም መጽሐፉ ላይ የሌለ ነገር በማነብነብ መሆኑን ቀጥሎ በተናገሩት ውስጥ መመልከት ይቻላል፤

> ሙሴ በግ እየጠበቀ ነው፡፡ አንድ ቀን ተራራው ላይ እሳት ይነዳል፡፡ ሙሴ ከሩቅ አየ ደነቀው፤ ምን ደነቀው መሰላችሁ? <u>ተራራው ላይ ሌሎች ሁሉ እየተቃጠሉ ተራራው እየጨሰ እሳቱ እያቃጠለው</u> ጳጦስ የተባለች አንዲት ዕፅ በተራራው መሃል ሆና <u>ሌሎቹ ሲነዱ ሌላው ሲቃጠል</u> ያቺ ጳጦስ የተባለችው ቅጠል ግን÷ ተክል ግን በዛ አንዳች እሳት አያቃጥላትም፡፡ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ቢመለከት ሙሴ ተገርሞ ወደ ተራራው ተጠጋ… (20፡01-20፡47 ደቂቃ - አጽንዖት የግል)፡፡

ይህን የመሰለ ታሪክ የት ላይ እንዳነበቡ ነግረውን ቢሆን መልካም ነበር፡፡ ቅዱሱ መጽሐፍ ላይ የሰፈረው ግን *«ሙሴም የዮቶርን የአማቱን የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር፤ ወደ ምድረ በዳ ዳር ቻም በጎቹን ነዳ፥ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ። የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል ታየው፤ እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ። ሙሴም፦ ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ»* የሚለው ብቻ ነው፡፡ የተራራው መቃጠል፣ መንደድና መጨስ ግን አልሰፈረም፡፡ የተጻፈውን ብቻ ማንበብ እና እሱን ማብራራት ለእግዚአብሔር ቃል ያለንን አክብሮት የምንገልጽበት መንገድ ነውና እባክዎ መምህር ይህን ያድርጉ (ዘጸአት 4÷1-3)፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ፤

> ሕዝቤን ልቀቅ ብለህ ለፈርኦን ንገረው፡፡ ምልክት እንዲሆንህ በዚህች ተራራ መጥታችሁ ትሰግዳላችሁ፡፡ <u>እኔም ሕግንና ሥርዓትን እሰጥሃለሁ አለው</u> ይላል ይህ በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ሦስት ቍጥር ዐሥራ ሁለት ላይ የምታዩት ነው

በሚል የተናገሩትንም መመልከት ይቻላል (21፡33-21፡53 ደቂቃ - አጽንዖት የግል)። ለምን እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም በመጽሐፉ ላይ ከተጻፈው ይልቅ እሳቸው ለሚናገሩት ትልቅ ግምት ይሰጣሉ። ቃሉ ላይ እንደሰፈረው መናገር በጣም ነው የሚቸገሩት፡፡[1] አሁንም *«እርሱም፦ በእውነት እኔ ከእንተ ጋር እሆናለሁ እኔም እንደ ላከሁህ ምልክትህ ይህ ነው ሕዝቡን ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ በዚህ ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር ትገዛላቸሁ አለ»* በሚል የሰፈረውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳለ ከመቀበል ይልቅ *«እኔም ሕግንና ሥርዓትን እሰጥሃለሁ»* የሚል ጨምረውበት *«አለው ይላል»* ሲሉ ተሰምተዋል።

በዐዲስ ኪዳን ታቦት የበለጠ ክብር ነው የተሰጠው

ቤተ ክርስቲያናችን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት[2] ከሚለይዋት ነገሮች ውስጥ አንዱ ታቦትን መያዟ ነው። በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ታቦት ተቀባይነት የሌለው÷ አሁን የዐዲስ ኪዳን የአገልግሎት ዘመን በመሆኑና÷ የዐዲስ ኪዳን አገልጋዮች (የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት) ታቦት አለመጠቀማቸውና ታቦትን መጠቀም አስፈላጊ ስለመሆኑ አለመጻፋቸውን መሠረት በማድረግ ነው።

> «መምህሩ» ግን ከዚህ ለየት ሐሳብ አላቸው፤ እሱንም፡-
>
> በዐዲስ ኪዳን ስንመጣ ታቦት ጭራሽ የበለጠ ክብር ነው የተሰጠው። ተመልከቱ እግዚአብሔር የበለጠ ክብር ሰጥቶታል። ሁለተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ሦስት ላይ እዩ የበፊቱ የብሉይ ኪዳን ሕገ ታቦት በክብር ከሆነ የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት ታቦቱ ደግሞ እጅግ በክብር ነው ይላል፤ ተመልከቱ በክብር ነው...

በሚል አቅርበውት ነበር (32፡40-33፡10 ደቂቃ)። ሐዋርያው ጳውሎስ አሁን እርሳቸው በጠቀሱት ስፍራ ላይ የታቦትን ክብር ከፍ ከፍ አድርጎት ይሆን? ምንባቡ እንዲህ ይላል፤

ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንምና፤ እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለዐዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣልና። ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለ ተሻረው ስለ ፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ፥ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ÷ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር ሊሆንልን? የኵነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ፥ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር አብዝቶ ይበልጣልና። ያ የከበረ እንኳ እጅግ በሚበልጠው ክብር ምክንያት በዚህ ነገር ክብሩን አጥቶአልና። ያ ይሻር የነበረው በክብር ከሆነ፥ ጸንቶ የሚኖረውማ እጅግ ይልቅ በክብር ሆኖአልና - (2ኛ ቆሮንቶስ 3÷5-11)።

ሐዋርያው በዚህ ክፍል ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸው (በድንጋዮች የተቀረጸው ትእዛዛቱ መሆናቸውን የተቀረጸበት ድንጋይም ጽላቱ መሆኑን ግልጽ ነው)[3] አገልግሎት የሞት ነው አለ እንጂ አሁን በበለጠ ክብር አለ አላለም። ከዚህም ሌላ አገልግሎቱን የኵነኔ ሲል ነው የጠራው። አሁን በክብር አለ ያለው «የመንፈስ አገልግሎት»፣ «የጽድቅ አገልግሎት» ብሎ የጠራው ሲሆን እሱም በዐዲስ ኪዳን በክርስቶስ ኢየሱስ የተገለጸውና በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ብርታት እየሄደ ያለው አገልግሎት እንጂ ታቦት አለመሆኑ ይታወቃል።

እርሳቸው ስሙንም ሳያነሡት ያልፉት አንድምታ ትጓሚው፤ «ሕይወት የሚገኝባት ሕገ ጽድቅ ወንጌልማ ምን ያህል ትከብር ይሆን? በዚህ ፍጹም ክብር ባነጻጸሯት ጊዜ ከብራ የነበረች ሕገ ኦሪት እንዳልከበረች እስከትሆን ድረስ። ኃላፊው ሕገ ኦሪት ክብር ካገኘ ባለ ማለፍ ጸንቶ የሚኖረው ሕገ ወንጌልማ ምን ያህል ክብር ያገኘ ይሆን? አንድም (ኃላፊ) ይላል ኃላፊውን ሕገ ኦሪትን የያዘ

---

[1] በኪዳነ ምሕረት ቁጥር 10 ላይ «ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ» የተሰኘው የመምህሩ የኑፋቄ ስብከት በተፈተሸበት ጊዜም ተመሳሳይ ችግር እንዳለባቸው ቀርቦ ነበር።

[2] ከሌሎች ተብሎ በዚህ ስፍራ ላይ የቀረበው ከወንጌላውያንና ከካቶሊክ ጋር ብቻም ሳይሆን ከእኅት አብያተ ክርስቲያናትም ጭምር ነው።

[3] አንድምታው ላይ «በድንጋይ ሰሌዳነት ስለ ተጻፈች ለዚያች ለሕገ ኦሪት ክብር ከተደረገላት» የሚለውን መመልከት ይቻላል።

ክብር ካገኘ ባለ ማለፍ ጸጉዶ የሚኖረው ሕገ ወንጌልንማ የያዘ ምን ያህል ክብርን ያገኝ?» የሚል ጥያቄ በማንሣት ሕገ ኦሪት ኃላፊ መሆኑን ደጋግሞ ያስነብባል፡፡ ታዲያ ምነው «መምህሩ» ያልተጻፈ አነበቡሳ? ቢባል እሱማ ልማዳቸው ስለሆነ የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡

ታቦትና ጣዖት

ብዙዎች ታቦት አስፈላጊ መሆኑን አስረግጠው ለመናገር ሲፈልጉ ታቦትን የሰጠው እግዚአብሔር ነው እግዚአብሔር ደግሞ ጣዖት የሚሆንን ነገር አይሰጥም ሲሉ ይሰማሉ፡፡ «መምህሩም» ከዚህ ሐሳብ ጋር በተገናኘ፤

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ጣዖት ይሰጣል? ይሰጣል ይመስላችኋል?

ብለው ሕዝቡን ጠይቀው ነበር (34፡47-34፡50 ደቂቃ)፡፡ ከዚህም ጋር በማያያዝ፤

> ታቦትና ጣዖት ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፡፡ የሚያገናኝ ሰው ሲመጣ ራሱ እግዚአብሔር እነሆ እጅግ አድርጎ በዚህ ሰው ያዝናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ ስትመለከቱ ስለ እግዚአብሔር ታቦት ሲናገር ‹ወመኑ ዘይዴምር ታቦተ እግዚአብሔር ውስተ ቤተ ጣዖት› ይላል፡፡ ይህ በሁለተኛ ቆሮንቶስ 6÷16 ላይ ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ጽድቅ ከአመጽ ጋር ምን ተካፋይነት አለው? ጽድቅና አመጽ ይስማማሉ? አይስማሙም፡፡ የሚያምንም ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔር ታቦት ከጣዖት ጋር ምን ኅብረት አለው? ተመልከቱ አሁን እዚህ ጋር ተቃራኒ ነገሮችን ነው ያየነው፡፡ እዚህ ጋር ለምሳሌ ማንን አየን? (ቀኝ እጃቸውን ወደ ቀኝ ዘርግተው) ክርስቶስን አይደለም? በዚህ ክርስቶስን አየን፡፡ በዚህ ደግሞ ምንን ነው ያሳየን (ግራ እጃቸውን ወደ ግራ ዘርግተው) ሰይጣንን፡፡ ክርስቶስና ሰይጣን ይስማማሉ? አይስማሙም፡፡ ቀጥሎ የሚያምን አለ፤ የሚያምነው ከማን ወገን ነው? ከክርስቶስ፡፡ የማያምን አለ፤ የማያምነው ከማን ወገን ነው? ከሰይጣን፡፡ ብርሃን አለ፤ ብርሃን ከየት ወገን ነው? ከማን ወገን ነው ብርሃን? ከክርስቶስ፡፡ ጨለማስ? ብርሃን የተባለው ከኢየሱስ ነው፡፡ ዮሐንስ 8÷21 ላይ ‹እነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም› ይላል፡፡ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ አለ፡፡ ሰይጣንን ደግሞ ምን ብሎታል? የጨለማው ገዢ ብሎታል፡፡ ተመልከቱ ቀጥሎ ደግሞ የማይስማሙ ነገሮችን ያስቀመጠው ምንን ነው? ታቦትንና ጣዖትን፡፡ ታቦት ከማን ወገን ነው? ከክርስቶስ፡፡ ጣዖትስ? ከሰይጣን፡፡ ሊስማማ አይችልም፡፡… ቅድም የተመለከትነው የእግዚአብሔር ታቦት የሚለውን እነርሱ መቅደስ ከጣዖት ምን ኅብረት አለው ብለው ታል፡፡ መቅደስ ከጣዖት ጋር ከሆነ መሆን የነበረበት የእግዚአብሔር መቅደስ ከሰይጣን መቅደስ ጋር ነው፤ እንደሱ አይደለም፡፡

የሚለውን ንግግር ያደርጋሉ (34፡54-37፡33፡፡ 63፡49-64፡09 ደቂቃ)፡፡ እርሳቸው እንዳሉት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ጣዖትን አይሰጥም፡፡ ነገር ግን እርሱ ለበጎ ዓላማ የሰጣቸውን ነገር የሰው ልጆች ግን ጣዖት ኤድርገው ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ክፉ ልብ አላቸው፡፡ ለዚህም በምድረ በዳ ሳሉ በጥፋታቸው እባቦች ተለቀውባቸው በእባብ እየተነደፉ ሲሞቱ ከዚያ ለመዳን በዓላማ ተደርጎ ተሰቅሎ የነበረውን የንሐስ እባብ ሕዝቅያስ ተነሥቶ ነሑሽታን ብሎ ሰባብሮ እስከሚጥለው ድረስ ያጥኑለት እንደ ነበር መመልከቱ ይበቃል (2ኛ ነገሥት 18÷4)፡፡ ሕዝቅያስ የነሐስ እባቡን የሰባበረው ምን ኤድርጎት ነው? ጣዖት በመሆኑ አይደለምን? ሕዝቅያስ ይህን ያደረገው በዚህ ዘመን ቢሆን ኖሮ ታላቁ አምላክ እግዚአብሔር ለታላቁ ሰው ለሙሴ የሰጠውን ቅዱስ የንሐስ እባብ የሰበረው ሃይማኖት ለመበረዝ የተነሣ መናፍቅ በመሆኑ፣ በዚህ ላይ ቤተ መቅደስ ውስጥ የገባ ሰው በመሆኑ የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ፣ ግእዝ ተናገሪ ጴንጤ፣ ተሃድሶ እና ሌሎችንም ብዙ ስሞችን በተሸከመ፣ በጋዜጣና በመጽሔትም በወጣ፣ ከአምልኮ ስፍራም በተገለለ ነበር፡፡

ሌላው ሐዋርያው ጳውሎስ ታቦትን ከጣዖት ጋር ማን ያኖራል? ያለው ታቦትን በተመለከተ ነው የተባለው የመጽሐፉን ዐውዳዊ ፍቺ ያለመከተል ችግር ነው፡፡ *«ከማያምኑ ጋር በማይመቻ አካሄድ አትጠመዱ»* በሚል የሚጀምረው ሐዋርያው ምክንያቱንም የተለያዩ ነገሮች እያነጻጸረ ያሳያቸዋል፤ አትጠመዱ እያላቸው ያሉትን ክርስቲያኖችን እናንተ *«ጽድቅ»፣ «ብርሃን»* ናችሁ ሲላቸው በውስጣችሁ ደግሞ ክርስቶስ አለ፣ አማኞች ናችሁ ስለዚህ እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ የሚል ሐሳብ ያቀርብላቸዋል፡፡ የማይመች አካሄድ ስለሆነ አትጠመዱ የተባለለትን ደግሞ *«አመጽ»* ነው፣ *«ጨለማ»* ነው፣ የእርሱ ጌታና በውስጡ የነገሠው ቤልሆር ነው፣ ስለዚህ በዚያ ያሉት

የማያምኑና ጣዖት አምላኪዎች ናቸው የሚል ሐሳብ እያቀረበ ነው፡፡ ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው ሐዋርያው ይህን ሐሳቡን «እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፦ በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። ስለዚህም ጌታ፦ ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኩሰንም አትንኩ ይላል፤ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፦ እኔም እቀበላችኋለሁ፥ ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል» በሚል ማጠቃለሉን ስንመለከት ነው፡፡ «መምህሩ» ግን ይህን የመጨረሻውን ሐሳብ ቆርጠው ትተውታል፡፡ ምክንያቱም እርሳቸው ሊሉ የፈለጉትን እንዳይሉ ይከለክላቸዋልና፡፡

«ይላል»

ስብከቱን እንድመለከተው የሰጠኝ ወዳጄ ስብከቱን በተመለከተ አስተያየቱን ሲሰጥ «መምህሩ» ያልተጻፈ እያነበቡ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተጻፈ ለማስመሰል «ይላል» የሚሉት ስለገረመው «ደግሞኮ ይላል የሚሉት ነገር ይገርማል» ብሎኝ ነበር፡፡ በእርግጥም ሰው ያልተጻፈ እያነበበ «ይላል» ለማለት ምን ዓይነት ድፍረት ይኖራል? መምህሩ ግን ይህ ችግር የለባቸውምና መጽሐፍ ቅዱስ የማይለውን ይላል ሲሉ በድፍረት ሰብከዋል፡፡ የእርሳቸው ሐሳብና የመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ምን ያህል የተራራቀ እንደሆነ አንባቢው በራሱ ይመለከት ዘንድ ሁለቱንም ሐሳቦች ጎን ለጎን ማስቀመጡ የተሻለ ነው፤

መጽሐፍ ቅዱስ - 2ኛ ቆሮንቶስ 6፥16	«መምህር» ዘበነ
ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፤ በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ፡፡	ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ምን አለ? ማን ነው ታቦትን ከጣዖት ጋር የሚያኖር? <u>ማን ነው ታቦትን ጣዖት የሚል? የራሱ የጣዖቱ ፍዳ በእሱ ላይ ይደርሳል</u> <u>ይላል</u> (42፡09-42፡23 ደቂቃ - አጽንዖት የግል)፡፡

<u>ታቦት በሰማይ</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ አንድ ታቦት እንዲኖር ፈለገ ከዚያ በኋላ ታቦት እንዲሠራ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም በሚል ለሚነሣው ሐሳብ መልስ ለመስጠት የተቸገሩት ወንድሞቻችን በራእይ ዮሐንስ ምዕራፍ ፲፩ ቁጥር ፲፱ ላይ «በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ» ተብሎ የተጻፈውን መነሻ በማድረግ፤

ታቦት እንኳን በምድር በሰማይ ላይ ያለ ነው (45፡14-45፡35 ደቂቃ) ይላሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች ወይ የቤተ ክርስቲያናቸውን መጽሐፍ አያውቁትም አልያም የገዛ መጽሐፋቸውን አይቀበሉም ይሆናል እንጂ በራእይ ዮሐንስ አንድምታ ላይ *«ሕጉን ጠብቃ የምትኖር ምእመንም መንግሥተ ሰማያትን ወርሳ ከብራ»* እንደታየች ነው የተብራራው፡፡[1]

ከዚህም ሌላ «አቡቀለምሲስ ዮሐንስ በራእዩ <የቃል ኪዳኑ ታቦት በሰማይ ታየ> ብሎ የመሰከረለት ታቦት ጽዮን ሳትሆን አማናዊት ጽዮን ድንግል ማርያም ናት፡፡ አማናዊት ጽዮን ድንግል ማርያም ሰው እንደ መሆኗ ሞታ ተቀብራለች፤ ይሁን እንጂ ተቀብራ አልቀረችም እንደ ልጇ እንደ ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን ተነሥታ ወደ ሰማይ አርጋለች፡፡ በልጇ በወዳጇ በክርስቶስ ቀኝ ተቀምጣ

[1] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ መጻሕፍተ ሠልስቱ ዐዲሳት ንባቡና ትርጓሜው (ዐዲስ አበባ፣ 1989) ገጽ 423 423 ይመልከቱ፡፡

ዮሐንስ ያያት ድንግል ማርያም ናት ታቦት ቢሆን በሰው አምሳል ተቀምጦ አይታይም ነበርና»[1] የሚል አስተያየት የሚሰጡ ሰዎች አሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሰዎቹ ከቤተ ክርስቲያናቸው ትምህርት እና እርስ በእርሳቸው እንኳ የማይስማሙ መሆናቸውን ፍንትው አድርጎ ያሳያልና በቅድሚያ እርስ በእርሳችሁ ተስማሙ ማለቱ መልካም ሳይሆን አይቀርም፡፡

ካህኑ መልአክ

ምናልባት ርዕሱን ሲመለከቱ በቤተ ክርስቲያናችን የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ ሰዎችም መልአክ ተብለው ይጠራሉ የሚለውን አስታውሰው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ርዕስ የምንመለከተው «መምህር» ዘበነ ሥልጣነ ክህነት ስለ ሰጡት መልአክ ነው፡፡ የመምህሩን ሐሳብ እነሆ፤

> በሰማይ መቅደስ እጣን አለ፤ ስለ ካህናት አታዩም እንዴ? ራእይ ዮሐንስ ምዕራፍ ስምንት ላይ ካህኑ መልአኩ ሲያጥን መቅደስ ውስጥ… (56፡24 - 56፡30 ደቂቃ)፡፡

ይህን ያሉት *«ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሰዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሰዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ»* የሚለውን ተመልከተው ነው (ራእይ 8÷3-4)፡፡ በዚህ መልእክት ውስጥ መልአኩ የክህነት ሥልጣን እንዳለው የተገለጸ ነገር የሌለ ሲሆን የሠራውም የክህነት ሥራ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የዕጣን ማቅረቢያ ቢኖርም የካህናት ተግባር በቤተ መቅደስ ውስጥ ጥና ይዘው ዕጣን ማጠን አልነበረም፡፡ የዕጣን ማቅረቢያው በካህኑ እጅ ሆኖ ዕጣን የሚቀርብበት ሳይሆን ተቀማጭ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አሠራሩ በተናገረበት ስፍራ *«የዕጣን መሠዊያውን ሥራ፤ ከግራር እንጨት ሠርተህ፡፡ ርዝመቱ አንድ ክንድ፥ ስፋቱም አንድ ክንድ፥ አራት ማዕዘን ይሁን፤ ከፍታውም ሁለት ክንድ ይሆናል፤ ቀንዶቹም ከእርሱ ጋር በአንድነት የተሠሩ ይሁኑ። ላይኛውንና የግድግዳውንም ዙሪያ ቀንዶቹንም በጥሩ ወርቅ ትለብጠዋለህ፤ በዙሪያውም የወርቅ ከፈፍ ታደርግለታለህ። ከከፈፉም በታች ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ሠርተህ ግለት። በዚህና በዚያ በሁለቱ ጎን ታደርጋቸዋለህ፤ ለመሸከምም የመሎጊያዎች ሰፍራ ይሁኑ። መሎጊያዎቹንም ከግራር እንጨት ሠርተህ፥ በወርቅም ለብጣቸው። በምስክሩ ታቦት አጠገብም ካለው መጋረጃ በፊት ታኖረዋለህ ይህንም አንተን በምገናኝበት ከምስክሩ በላይ ባለው በስርየት መክደኛ ፊት ታኖረዋለህ። አሮንም የጣፋጭ ሽቱ እጣን ይጠንበት፤ በማለዳ በማለዳ መብራቶቹን ሲያዘጋጅ ይጠነው»* የተባለ ሲሆን በዚህ ውስጥ ዕጣን መሠዊያው አንድ ሰው ይዞት የሚይነቀሳቀስ መሆኑን እና ተቀማጭ መሆኑን መረዳት ይቻላል (ዘጸአት 30÷1-7)፡፡

የካህናቱ *ሥራ* ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ የሚሆነውን መሥዋዕት ማቅረብና ዘወትር ስለ ሕዝቡና ስለ ራሳቸው ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ምሕረትን መለመን ነው፡፡ ዕጣን ማቅረብ ካሏቸው *ሥራዎች* ውስጥ አንዱ እንጂ ቀዳሚው ባለመሆኑ የዕጣን ማቅረቢያ የያዘ ሁሉ ካህን የሚባልበት አግባብ የለም፡፡ ከዚህም ሌላ መላእክት ካህናት መሆን ቢችሉ ኖሮ እነርሱን ሞት የሚገዛቸው ስላልሆነ አንድ መልአክ ብቻ በበቃ ነበር፡፡ ነገር ግን መላእክት ካህናት መሆን ስለማይችሉ «ለሚሻል ኪዳን ዋስ» የሆነው ክርስቶስ እስከሚመጣ ድረስ ሞት በአገልግሎታቸው እንዳይቀጥሉ የከለከላቸው ሰማንያ ሦስት ሊቀ ካህናት ተሾመው ነበር፡፡[2] ስለዚህ መምህር በቤተ ክርስቲያን ትምህርትም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ውስጥ የሌለ እንግዳ ትምህርት ማስተማርዎ ከሰውም ሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያሰጥዎ ዋጋ የለምና መጽሐፍ ቅዱሱ የሚለውን ብቻ ያስተምሩ፡፡

---

[1] «ገድል ለመናፍቃን ገደል» መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን (ገጽ 119-120)፡፡ «ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ» ንቡረ እድ ኤርሚያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ (ገጽ 82)፡፡

[2] ራእይ አሳታሚ፣ የዐዲስ ኪዳን ማብራሪያ (2006 - ዐሥራ አንደኛ ዕትም) ገጽ 568፡፡

<u>የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል?</u>

የቃል ኪዳኑ ታቦት የት ነው ያለው? የሚለው ለብዙዎች አሁንም ድረስ ልብን የሚያሳርፍ መልስ ያላገኘ ጥያቄ ነው፡፡ ምክንያቱም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የታቦቱን መጨረሻ በግልጽ የማይናገር በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በመነሣት የተለያዩ መላምቶች ይሰጣሉ፤ ከሚሰጡት መላምቶች አንዱ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል የሚለው ነው፡፡ «መምህሩ»ም በዚህ ሐሳብ የሚስማሙ በመሆናቸው ከአንድ እናት፤

> መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተሸሯል የሚል አለ፡፡ ይሄውም ምዕራፉንና ቁጥሩን አንተ መምህራችን ታስታውሰኛለህ ከአሁን በኋላ አያስታውሱትም ከአሁን በኋላ ትተውታል የሚል አለ፡፡ ከዚህ በኋላ አያስታውሱትም ትተውታል [የሚለው] እሱ በጣም እያስኬዳቸው በዚህ ብዙ ሰው አታለውበታል፤ የታቦትን መሻር፡፡

ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ፤

> በጣም ጥሩ… ጥቅሱ ኤርምያስ 3÷16 ነው፡፡ ኤርምያስ እንዲህ አለ፡- የእስራኤል ልጆች ከእንግዲህ በኋላ የእስራኤል ታቦት ብለው አይጠሩም አይሸቱም አይፈልጉትም፡፡ ለምን? ምክንያቱም ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ ይሄዳል፡፡ ተመልከቱ ታቦቱ እስከ ሰሎሞን ዘመን ነው የኖረው የሰሎሞን ልጅ ሮብአም በነገሠ ጊዜ የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፍሏል፡፡ ስለዚህ ዳዊት ቀደም ይሄንን አይቶ ስለ ነበር በመዝሙር 67÷31 ላይ ምን ብሏል? ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች አለ፡፡ ሰሎሞን ከማከዓ የወለደው ልጅ ምኒልክ እስራኤል በሃያ ሁለት ዓመቱ ሄዶ በዘው በሊቀ ካህናቱ በሳዶቅ ቅብዓ ንግሥና ፈጽሞ የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ስለሚከፈል ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ሊቀ ካህናቱ አዛርያስና ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት የእስራኤል እነሆ ሊቃውንት የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ሆነው ሌዋውያን ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ፡፡ ስለዚህ ኤርምያስ ምን አለ? የእስራኤል ልጆች ከእንግዲህ በኋላ የእግዚአብሔር ታቦት ብለው አይጠሩም ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ ሄዷልና፡፡

የሚል ምላሽ ለመስጠት ደፍረዋል (59፡59-62፡09 ደቂቃ)፡፡ «መምህሩ» እዚህ ላይ ሁለት ስሕተቶችን ሠርተዋል፤

የመጀመሪያው ትንቢተ ኤርምያስ የሚለውን ትተው እርሳቸው ለማለት የፈለጉትን መጽሐፉን ተገን በማድረግ ተናግረዋል፡፡ ኤርምያስ ያለው *«<u>በበዛችሁም ጊዜ በምድርም ላይ በረባችሁ ጊዜ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በዚያ ዘመን</u>፦ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም ልብ አያደርጉትም፥ አያስቡትምም፥ አይሹትምም፥ ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም»* ነው (ኤርምያስ 3÷16 - አጽንዖት የግል)፡፡

መጽሐፉ ታቦቱን የማይፈልጉበትን ዘመን የገለጸው *«በበዛችሁም ጊዜ በምድርም ላይ በረባችሁ ጊዜ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በዚያ ዘመን»* በሚል ነው እንጂ *«ወደ ኢትዮጵያ ስለተወሰደ ነው»* በሚል አይደለም፡፡ እሳቸው ግን ይህ ሐሳብ ሊናገሩ ለፈለጉት መልእክት አመቺ ባለመሆኑን ምክንያት ቄርጠው በመጣል የሚፈልጉትን ብቻ ወስደው ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ ስለተወሰደ ነው የሚል ሐሳብ አክለውበታል፡፡ ይህ ደግሞ «መምህሩ» መጽሐፍ ቅዱስን ለገዛ ፈቃዳቸው እንደሚያጣምሙ ግልጽ ያደርጋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል የሚለው ሐሳባቸው ነው፡፡ ለዚህ ሐሳብ ይረዳ ዘንድ የሂሳብ ስሌት ማስቀመጡ እና የቤተ ክርስቲያኒቱ መጻሕፍት ስለ ታቦቱ ፍጻሜ ምን ይላሉ? የሚለውን ማስነበቡ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በክብረ ነገሥትም ሆነ የክብረ ነገሥት አፍ በሆኑት ሰዎች እምነት መሠረት የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢትዮጵያ ይዞት የመጣው ቀዳማዊ ምኒልክ ነው፡፡ «መምህሩ» ምኒልክ አባቱ ነው ወደሚባለው ወደ ንጉሥ ሰሎሞን የሄደው በ22 ነው ያሉትንና በዚያም ለሦስት ዓመታት ከተቀመጠ በኋላ ወደ አገሩ ሲመለስ ታቦቱን ይዞ መጥቷል የሚለውን ትርክት መሠረት በማድረግ የሂሳብ ስሌት ሲሠራ በእግርጥ ሰሎሞን ይህን ያህል ጊዜ ተቀምጧልን? የሚል ጥያቄ ይፈጥራል፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሆን ዘንድ ቀጥሎ ያለውን የሂሳብ ስሌት ይመልከቱ፤

- ሰሎሞን በነገሠ በአራት ዓመት ከሁለት ወሩ ቤተ መቅደስ ለመሥራት መሠረት አኖረ (2ኛ ዜና መዋዕል 3÷1-2) 4 ዓመት ከ2 ወር፣
- የቤተ መቅደሱ ሥራ ሰሎሞን በነገሠ በ11 ዓመት ከስምንት ወር ተጠናቀቀ (1ኛ ነገሥት 6÷36-37) ሥራው የወሰደው ጊዜ ሰባት ዓመት ከስድስት ወር፣
- ከዚያ በኋላ ሰሎሞን የራሱን ቤተ መንግሥት አሳነጸና በነገሠ በ20 ዓመት አጠናቀቀ (1ኛ ነገሥት 9÷10፡፡ 2ኛ ዜና መዋዕል 9÷10-28፡፡) ሥራው የወሰደው ጊዜ ዐሥራ ሦስት ዓመት፣
- ሰሎሞን ከዚያ በኋላ በማከታተል አገርና ለመንግሥት የሚጠቅሙ ሥራዎችን አሠርቷል (1ኛ ዜና መዋዕል 8÷1-18፡፡ 1ኛ ነገሥት 9÷10-28) ሥራዎቹ በምን ያህል ጊዜ እንደ ተጠናቀቁ አልተጠቀሰም፡፡
- ንግሥት ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት የሄደችው ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር፡፡ የቤተ መቅደሱን ሥራና የአገልግሎቱን ሥርዓት አድንቃለች፡፡ የቤተ መንግሥቱን ወጭና የውስጥ ድርጅት ጎብኝታለች (1ኛ ነገሥት 10÷1-13፡፡ 2ኛ ዜና መዋዕል 9÷1-12) የጉብኝቱ ጊዜ ምን ያህል እንደሆነ አልተጠቀሰም፡፡ ነገር ግን ኢየሩሳሌም በገባች ዕለት ከሰሎሞን ፀነሰች ተብሎ ቢታሰብና የእብነ መሊክ (የቀደማዊ ምኒልክ) መወለጃ ጊዜ ዘጠኝ ወር ቢደመርና እንዲሁም
- እብነ መሊክ (ቀዳማዊ ምኒልክ) በ22 ዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ስለሚባል ሃያ አምስት ዓመት ሲደመርበት አምሳ ዓመት ከሰባት ወር ይሆናል፡፡ ነገር ግን የሰሎሞን የግዛቱ ዘመን አምሳ ዓመት ከሰባት ወር ሳይሆን አርባ ዓመት ብቻ እንደ ነበር የተረጋገጠ ነው፡፡[1]

ከዚህም ሌላ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጻሕፍት ታቦቱን በተመለከተ የሚግባቡ አይመስሉም፡፡ ቀደም ሲል እንደቀረበው ክብረ ነገሥት የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል የሚል ሐሳብ ሲያቀርብ (ገጽ 48)፤ መጽሐፈ ዕዝራ ካልእ ምዕራፍ 1 ቁጥር 54 እና ዕዝራ ሱቱኤል ምዕራፍ 9 ቁጥር 21-22 ላይ ታቦቱ ከሌሎቹ የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች ጋር አብሮ በምርኮ ወደ ባቢሎን እንደ ተወሰደ ይናገራል፡፡ ይህ የሆነው ከሰሎሞን ሞት ከ334 ዓመታት በኋላ ማለት ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ በተረፈ ኤርምያስ ምዕራፍ 8 ቁጥር 13 ላይ ባሮክና ኤርምያስ የቤተ መቅደሱን ዕቃ ለምድር እንደሰጧት እና ምድር እንደ ዋጠችው ይናገራል፡፡ ይህ ሁሉ እርሱ በእርሱ የማይስማማ ሐሳብ ቤተ ክርስቲያናችን የእኔ ናቸው በምትላቸው መጻሕፍት ውስጥ ያለ መሆኑን አናበቢው ልብ ይበል፡፡[2]

ከዚህ ሌላ «የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000» የተሰኘው መጽሐፍ ምኒልክ «ለ25 ዓመታት /982-957/ ከነገሠ በኋላ በ58 ዓመቱ ዐረፈና ከአክሱም ከተማ በስተምዕራብ በኩል በሚገኘው ቦታ በእናቱ መቃብር አጠገብ ተቀበረ» ይላል (ገጽ 9)፡፡ ይህ ደግሞ ሌላ የታሪክ ክፍተት ነው፡፡ ምክንያቱም አባቱ ጋር በ22 ዓመቱ ሄዶ ለ3 ዓመታት ከተቀመጠ በኋላ ተመለሰ ከተባለ 25 ዓመታት ሆኖታል ማለት ነው፡፡ መጽሐፉ እንደሚለው ከአባቱ ከሰሎሞን እንደ ተመለሰ «ወዲያውም ንግሥቲቱ ዙፋንዋን፣ ሥልጣነ መንግሥቷን ለምኒልክ አስረክበ አነገሠችው»፡፡ የሰሎሞን የንግሥና መጨረሻ 931 ከሆነና በንግሥናው ላይ የቆየው ለ40 ዓመታት ከሆነ ወደ ንግሥናው የመጣው በ971 ነው ማለት ነው፡፡ ልጁ ምኒልክ የነገሠው በ982 ነው ከተባለ ሰሎሞን ወደ ንግሥናው ሳይመጣ ቤተ መንግሥቱንም ሆነ ቤተ መቅደሱን ሳይገነባ ከንግሥት ሳባ (ማክዳ) ጋር ሳይገናኝና ምኒልክም ሳይወለድ ቀዳማዊ ምኒልክ ንጉሥ ሆኖ ነበር ማለት ነው፡፡

[1] «ኢትዮጲስ» 2ኛው ግርማ ዘውዴ (ገጽ 84-85)፡፡ «ጮራ» መንፈሳዊ መጽሔት ቁ. 4 (ገጽ 15)፡፡ «ገድል ወይስ ገደል?» መምህር ጌታቸው (ገጽ 150-151)፡፡

[2] ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን (ዐዲስ አበባ፣ 2007 ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 63-64፡፡

ከዚህ ሌላ ደግሞ መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ በምዕራፍ ፣ ቁጥር 3-4 የቃል ኪዳኑ ታቦት በኢዮስያስ ዘመን ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደ ነበረ ይገልጻል፡፡ ይህም ታቦቱ ተሰረቆ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነበር ከሚባልበት ዘመን 359 ዓመት ዘግይቶ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ሐሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ጋር የሚስማማ ቢሆንም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ጋር ግን ተግባቦት እንደሌለው ግልጽ ነው፡፡

<u>ታቦት ለምን በዛ?</u>

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሚለያት የቃል ኪዳኑ ታቦት እኔ ጋ ማለቷ ብቻም ሳይሆን እንግዳ የሆኑ ታቦታትን በብዛት ይዛ በመገኘቷ ነው፡፡ በእጇ ላይ ያለው የታቦት መጠን ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የሚመጣ በመሆኑ አሁን ምን ያህል ታቦት እንዳለ ለማወቅ አስቸጋሪ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ቀደም ሲል እንደተባለው አሁን አሁን በእያንዳንዱ ደብር ሁለት እና ከዚያ በላይ ታቦት እንጂ ከዚያ በታች ለማግኘት አይቻልምና፡፡[1] ለምንድን ነው ታቦት የበዛው ለሚለው ጥያቄ ሰዎች የተለያየ መልስ ሲሰጡ ይሰማሉ፡፡ ለዚህም ይረዳናል የሚሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይጠቅሳሉ፡፡ «መምህሩም» ይህ ጥያቄ ቀርቦላቸው ሲመለሱ፤

> ታቦት ለምን በዛ? አይደለም ጥያቄው÷ መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ስንት ነበር? አንድ፤ ለምን በዛ? ምን መልስ አላቸው ለዚህ? እግዚአብሔር አምላክ <u>የዚያን ጊዜ ታቦት የሰጠው ለግማሽ ሚልዩን ሕዝብ ነው</u>፡፡ አሁን ደግሞ እየበዛ መጥቷል፡፡ እንደገና እግዚአብሔር ደግሞ ያዛል በተለያየ ምክንያት የሚያዘው አለ፡፡ ይህ ትእዛዝ አንዱ ምን የሚል ትእዛዝ አለ? መሰለሽ በኢሳይያስ 56 ቁጥር 7 ላይ ለቅዱሳኖቼ በቤቴና በቅጥሬ የዘላለም ስም አሰጣቸዋለሁ፡፡ የዘላለም ስም በቤቴ፤ ታቦት ቤቱ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው፡፡ ታቦት ማለት ማደሪያ ማለት ነው፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እንዳዘዘ በዚሁ ዓይነት መልኩ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነው ባስልኤልን አልያብን እንዲሠሩ በዘጸአት 36 ቁጥር ፣ ላይ እግዚአብሔር መረጣቸው፡፡ <u>ዛሬም ድረስ እንግዲህ ታቦቱ ሕዝብ እስካለ ድረስ እየተሰየመ፣ እየተሰጠ ይኖራል ማለት ነው፤ እንደ ሕዝቡ ብዛት</u>፡፡

ብለዋል (66፡19-67፡16 - አጽንዖት የግል)፡፡ ምን መልስ አላቸው ለተባለው እነሆ መልሱ፡፡[2]

«እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ታቦታትም እየተባዙ በየግለሰቡ ቤት ሁሉ ሊቀመጡ ይገባል አለማለትዎ መልካም ነው፡፡ አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ እየተባዛ በሰዎች እጅ ውስጥ እንዲገባ መደረጉ አስፈላጊና ተገቢ የሆነ ቅዱስ ተግባር ነው፡፡ ቃሉ ለሰው የተሰጠበት ዐብይ ምክንያት÷ ሰው አንብቦት እውነትን እንዲያውቅና ወደ ዘላለም ሕይወት ለመግባት እንዲዘጋጅ ለማድረግ ነውና፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት ግን መጀመሪያውኑ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ተግባር ለመፈጸም የተሰጠ አይደለም፡፡ ስለዚህ እንዲባዛም ሆነ በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ካልሆነ በቀር÷ በተለያዩ ስፍዎች እንዲቀመጥ አልታዘዘም፡፡ የኢትዮጵያ ዝርግ ሰሌዳ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ መባዛት ጋር መነጻጸር ሳያስፈልገው÷ ለሥጋ ወደሙ መክበሪያ በሆነው አገልግሎቱ ብቻ በየቤተ ክርስቲያኑ መገኘቱ በራሱ ስሕተት የለውም፡፡ ታቦት ተብሎ መጠራቱና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሊባዛ ይችላል መባሉ ነው ስሕተት የሚሆነው»፡፡

---

[1] አብያተ ክርስቲያናት ብቻም ሳይሆኑ አንዳንድ የዕለት በዓላትም እንግዳ የሆኑ ቅዱሳን እየተጨመሩባቸውና ዐዳዲስ ታቦታት እየተደረቡላቸው የቀድሞው ክብረ በዓላቸው እየተረሣ በዐዳዲሱ ሲዋጡ ተስተውሏል፡፡ ለአብነትም በየወሩ በስድስት ይከበር የነበረው ኢየሱስን ማንሣት ይቻላል፡፡ ወር በገባ በስድስት የሚኖረው የኢየሱስ ክብር የፊዘዘ ብዙም ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን የማይሄድበት በመሆኑ ማንነቷ እና ምንነቷ የማትታወቅ በስም ግን አርሴማ የተሰኘች ሴት በኢየሱስ ላይ ድርብ በዓል ሆነ የተቀመጠች ቢሆንም እውነታው ተገልብጦ አሁን ኢየሱስ ደርብ እስከሚመስል ድረስ በስድስት ማን ነው? ቢባል አርሴማ እንጂ ኢየሱስ የሚል ለማግኘት አይቻልም፡፡ ለነገሩ ቀድሞም በስድስት የማን ክበረ በዓል ነው? ቢባል እኔ አላውቅም የሚል ማኅበረሰብ ነበር የነበረው፡፡

[2] ከዚህ በታች የሰፈረው ሐሰብ የተወሰደው በዲያቆን አግዛቸው ተፈራ ተዘጋጅቶ «አልተሳሳትንምን?» በሚል ርዕስ በጥር 2003 ታትሞ ከነበረው መጽሐፍ ከገጽ 57 ነው፡፡

ሌላው ደግሞ የዚያን ጊዜ ታቦት የተሰጠው ለግማሽ ሚልዩን ሕዝብ ነው ያሉት ነው፡፡ «መምህሩ» እንዲህ ማለታቸው ከግብፅ ነፃ የወጣውን ሕዝብ ቁጥር መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ ቁጥር ግማሽ ሚልዩን ብቻ ሆኖ የቀረ ሳይሆን በየጊዜው ይጨምር ነበር፡፡ ዳዊት ባዳረገው ቁጠራ ብቻ «ኢዮአብም የሕዝቡን ቁጥር ድምር ለንጉሡ ሰጠ፤ በእስራኤልም <u>ሰይፍ የሚመዝዙ ስምንት መቶ ሺህ ጽኑዓን ሰዎች ነበሩ፤</u> የይሁዳም ሰዎች <u>አምስት መቶ ሺህ ነበሩ</u>» የሚል ይነበባል (1ኛ ሳሙኤል 24÷9)፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሕዝቡ ከግማሽ ሚልዩን ብቻ ሳይሆን ከአንድ ሚልዩን በላይ የሆነ ቢሆንም ታቦቱ ግን አንድ ብቻ ነበር፡፡ «መምህር» ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ምነው አንድ ታቦት ሳይጨምር ቀረሳ? የሚያውቁት ነገር ካለ ቢነግሩን፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>

«መምህር» እስከ አሁን በቀረበው መሠረት ብዙ ሰው ስላሳሳቱ ንስሐ ይግቡና ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ያስተምሩ ዘንድ ጥሪ ይቀርብልዎታል፡፡ በዚህ በዐዲስ ኪዳን ዘመን የቤተ ክርስቲያን «መምህር» ተብለው መድረክ ማግኘትዎ ለሁላችን ራሱን ቤዛ አድርጎ የሰጠውን ክርስቶስ ኢየሱስን በመስበክ ብዙዎች ካሉበት የጥፋት ሕይወት በንስሐ ወጥተው የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ለማድረግ እንጂ የቀደውምን ኪዳን ሰባኪ እንዲሆኑ አይደለም፡፡ «ሙሴስ ከቀደሙት ትውልድ ጀምሮ በሰንበት በሰንበት በምኵራቦቹ ሲያነቡ በየከተማው እርሱን የሚሰብኩ አሉት» ተብሎ የተጻፈ በመሆኑ ስለ ሙሴ ሳይሆን ስለ መድኅናችን ስለ ክርስቶስ ብቻ ያስተምሩ (ሐዋርያት ሥራ 15÷21)፡፡

«ብሉይ» ወይም «አሮጌው» ኪዳን የተባለው የተሻለውና «ዐዲስ» የሆነው ኪዳን ስለ መጣ ሲሆን ሰዎች ሁሉ በዚህ በዐዲሱ ኪዳን የእግዚአብሔርን መንግሥት የማግኘትን መብት አግኝተዋል፡፡ የዐዲስ ኪዳን አገልጋዮች ቀዳሚና ብቸኛ ሥራቸው ይህን ዐዲሱን ኪዳን ለሰዎች ሁሉ ማወጅ ነው፡፡ እርስዎ ግን ሕዝቡን ሁሉ ወደ ኋላ በመጎተት ላይ ይገኛሉ፡፡

«መምህሩ» መጽሐፍ ቅዱሳዊ ላልሆነው ትምህርታቸው መጽሐፍ ቅዱስ የማይለውን እንደሚል በማስመሰልና የራሳቸውን ሐሳብ በመጨመር ሕዝብ ሲያሳስቱ መንጋውን እንዲጠብቁ ዐደራ የተሰጣቸውና በሥልጣን ላይ ያሉት አባቶች ዝም ማለታቸውስ ለምን ይሆን? ምናልባት እነርሱም የዚህ የኑፋቄ ትምህርት ተባባሪ ስለሆኑ ይሆን?

ሕዝቡም፤ በስም ትልቅነትና በተከታይ ብዛት እየተነሣሣ የሚሰማውን ሁሉ አሜን አሜን ከማለቱ በፊት እየቀረበለት ያለው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን አለመሆኑን መጽሐፉን በማንበብ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ አባቶች ዝም በማለታቸውና እና ሕዝቡም የቀረበለትን አሜን አሜን በሚል በመቀበሉ ምክንያት ብዙ የስሕተት ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ያለ ችግር ገብተዋል÷ አሁንም እየገቡ ነው÷ ለወደፊቱም ከመግባት የሚከለክላቸው ያለ አይመስልም፡፡

ጌታ ሆይ ሕዝብህን አስብ!!

<u>ታቦታችን</u>

ታቦታችን ሌባ የማይሰርቀው
ኢየሱስ ነው በደም የነገሠው
የፊደል ሕግ በመንፈስ ተሸሮ
ጀምረናል የዐዲስ ኪዳን ኑሮ
በመስቀል ላይ ሲሞት መጋረጃው ተቀዶ
አንድ አድርጎናል ጌታ ኢየሱስ ወርዶ
ልባችን ሆኖታል ማደሪያ መቅደሱ
ሰው በሥራው መቅደስ መቼ ይኖራል እሱ
ፊደል ሲገለን ኃጢአት እያሳየ
ታቦታችን ለእኛ ያለበደል ታየ
ሕጉን ጽፎ በልባችን ሰሌዳ
ሰጠን ዐዲስ ሕይወት ደመሰሰው ያን እዳ
ከወርቅና ከብር የማይቀጠቀጥ
በዋጋ በገንዘብ በሌላ የማይሸጥ
ከእንጨት ከድንጋይ ሰዎች የማይሠሩት
ጌታ ኢየሱስ ነው አማናዊው ታቦት
ከፍያለው ቱፋ


ኢየሱስ
እውነተኛ አማላጅ፤ ጻድቅ ፈራጅ
በቅርብ ቀን
ቴዎድሮስ ደመላሽ